# የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን

## የጤና ባለሙያዎች ምዝገባና የሙያ ስራ ፈቃድ አሰጣጥ አስተዳደርና ቁጥጥር መመሪያ

ሰኔ 2006 ዓ.ም

## ማውጫ

**<u>አርዕስት</u>** **<u>ገጽ</u>**

1. መግቢያ……………………………………………………………………2

2. ክፍል አንድ………………………………………………………………2
   1.1 አጠቃላይ……………………………………………………………2
      1.1.1 አጭር ርዕስ…………………………………………………2
      1.1.2 ትርጓሜ…………………………………………………………2
      1.1.3 የተፈጻሚነት ወሰን………………………………………………3
      1.1.4 ዓላማ……………………………………………………………3

2. ክፍል ሁለት
   2.1 የጤና ሙያን ስለመሰየምና የሙያ ስራ ፈቃድ ስመስጠት………………4
      2.1.1 ሙያ ስራ ፈቃድ አስፈላጊነት……………………………………4
      2.1.2 የሙያ ስራ ፈቃድ ለማገኘት መሟላት ስላለባቸው መስፈርቶች……4
      2.1.3 የሙያ ስያሜ ስለመስጠት…………………………………………5
      2.1.4 ስለሙያ ስራ ፈቃድ አሰጣጥ………………………………………5
      2.1.5 ከሙያ ስራ ወሰን ውጭ ስለመስራ…………………………………6
      2.1.6 ስለ አዳዲስ የሙያ ዘርፎች…………………………………………7
      2.1.7 የሙያ ስራ ፈቃድ ስለማሳደስ………………………………………7
      2.1.8 የሙያ ስራ ፈቃድ የማይሰራበት ጊዜ………………………………8
      2.1.9 በውጭ ሀገር የሰለጠኑ የጤና ባለሙያዎችን በኢንተርንሽፕ ስለመመደብ……………………………………………………………9
      2.1.10 ምትክ የሙያ ስራ ፈቃድ ስለመስጠት……………………………10

3. ክፍል ሶስት………………………………………………………………12
   3.1 ስለ አስተዳደራዊ እርምጃዎች……………………………………………12
      3.1.1 አስተዳደራዊ እርምጃ ስለመውሰድ…………………………………12
      3.1.2 የሙያ ስራ ፈቃድ የሚያሳግዱ ሁኔታዎች……………………………12
      3.1.3 ለሙያ ስራ ፈቃድ መሰረዝ የሚያበቁ ጥፋቶች…………………………13
      3.1.4 የሙያ ስራ ፈቃድ ስለመመለስ………………………………………13

4. የመተባበር ግዴታ…………………………………………………………13
5. ተፈፃሚነት የማይኖራቸው መመሪያዎች………………………………………13
6. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ…………………………………………………13
7. እዝል አንድ………………………………………………………………14
8. እዝል ሁለት………………………………………………………………15

## መግቢያ

የጤና ባለሙያዎች የሚሰጡት አገልግሎት ደረጃውን የጠበቀና ህብረተሰቡን ተጠቃሚ መሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የጤና ባለሙያዎችን ምዝገባና የሙያ ፈቃድ አሰጣጥና የቁጥጥር ስርዓትን ማጠናከር አስፈላጊ በመሆኑ፤

ባለስልጣኑም ከተሰጡት ስልጣንና ኃላፊነቶች መካከል በበቂ መጠን በገበያ ላይ የማይገኙ የጤና ባለሙያዎችንና ከውጭ ሀገር የጤና አገልግሎት ለመስጠት የሚመጡ ባለሙያዎችን መመዝገብና የሙያ ስራ ፈቃድ መስጠትና መቆጣጠር አንዱ በመሆኑ፤

በመሆኑም በኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 661/2002 አንቀጽ 55 ንዑስ አንቀጽ 3 እና ደንብ ቁጥር 299/2006 መሰረት ይህ መመሪያ ወጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## አጠቃላይ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ "የጤና ባለሙያዎች ምዝገባና የሙያ ሥራ ፈቃድ አሰጣጥ አሰተዳደርና ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 20 /2006" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 661/2002 አንቀፅ 2 ስር ለተቀመጡ ቃላት የተሰጡ ትርጓሜዎች እንደተጠበቁ ሆኖ በዚህ መመሪያ ዉስጥ፡-

   1. "የጤና ባለሙያ" ማለት የሰውን ጤና ለመጠበቅ ወይም አገልግሎት ለመስጠት በባለስልጣኑ እንደ ጤና ባለሙያ የተመዘገበ ሰው ነው፤
   2. "በበቂ መጠን በገበያ ላይ የማይገኙ የጤና ባለሙያዎች" ማለት ሀገራዊ ፍላጎትን ማሟላት ሳይቻል ሲቀር በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እጥረት እንዳለባቸው የሚቆጠሩ የጤና ባለሙያዎች ናቸው፤
   3. "የጤና ባለሙያ ምዝገባ" ማለት የጤና ባለሙያ ወደ ስራ ከመሰማራቱ በፊት የባለሙያውን መረጃና የሙያ ስያሜ በባለስልጣኑ የመረጃ ቋት ውስጥ መመዝገብ ማለት ነው፤
   4. "የሙያ ስራ ፈቃድ" ማለት የጤና አጠባበቅ አገልግሎት ወይም ሌሎች ተዛማጅ አገልግሎቶችን ለማበርከት እንዲችል ለጤና ባለሙያ የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው፤

5. "እክል" ማለት አንድ የጤና ባለሙያ የሙያ ስራውን ሲያከናውን ብቃቱን ወይም ሚዛናዊነቱን የሚያዛባ የአዕምሮ ወይም አካላዊ ሁኔታ ማለት ነው፤
6. "ተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ" ማለት ባለሥልጣኑ ባወጣው መመሪያ መሰረት ማንኛውም የጤና ባለሙያ በስራ ላይ እያለ በሙያው ያገኘውን እውቀትና ክህሎት ጠብቆ እንዲቆይ እና የሙያ ብቃቱን ለማጎልበት በየጊዜው የሚወስደው ሥልጠናና ሌሎች የሙያ ማጎልበቻ ስራዎች ነው፤
7. "እገዳ" ማለት ማንኛውም የጤና ባለሙያ ባለስልጣኑ ያወጣዉን የቁጥጥር ህግ በመጣሱ ወይም ባለማክበሩ ምክንያት ለተወሰነ ጊዜ ሙያዊ ስራውን እንዲያቋርጥ/እንዳያከናውን የማድረግ አስተዳደራዊ እርምጃ ነዉ፤
8. "ስረዛ" ማለት ማንኛውም የጤና ባለሙያ ባለስልጣኑ ያወጣዉን የቁጥጥር ህግ በመጣሱ ወይም ባለማክበሩ ምክንያት የጤና ባለሙያነት ስራ እስከ መጨረሻው እንዳይሰራ የማድረግ አስተዳደራዊ እርምጃ ነዉ፤
9. "ባለስልጣን" ማለት የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ነው፡፡

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በበቂ መጠን በገበያ ላይ በማይገኙ የጤና ባለሙያዎችና ከውጭ ሀገር የጤና አገልግሎት ለመስጠት በሚመጡ የጤና ባለሙያዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 4. ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማ፡-

1. የጤና ባለሙያዎችን ምዝገባና የሙያ ስራ ፈቃድ አሰጣጥ አስተዳደርና ቁጥጥር ስርዓትን በማጠናከር የህብረተሰቡን ደህንነት መጠበቅ፤
2. ህብረተሰቡ ሙያዊና ስነ ምግባራዊ ብቃት ባላቸው የጤና ባለሙያዎች የጤና አገልግሎት እንዲያገኝ ማስቻል፤
3. የጤና ባለሙያዎች ምዝገባና የሙያ ሥራ ፈቃድ አሰጣጥ አስተዳደርና ቁጥጥር ስራ በግልጽነትና ተጠያቂነት ስርዓት እንዲፈጸም ማስቻል፤

## ክፍል ሁለት
## የጤና ሙያን ስለመሰየምና የሙያ ስራ ፈቃድ
## ስለመስጠት

### 5. የሙያ ስራ ፈቃድ አስፈላጊነት

ማንኛውም ሰው ከባለስልጣኑ የሙያ ስራ ፈቃድ ሳያገኝ በጤና ሙያ መስክ መሰማራትና የጤና አገልግሎት መስጠት አይችልም፡፡

### 6. የሙያ ስራ ፈቃድ ለማግኘት መሟላት ስላለባቸው መስፈርቶች

ማንኛውም ሰው በጤና ሙያ ለመሰማራትና የሙያ ስራ ፈቃድ ለማግኘት የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡፡

1. በትክክል የተሞላ የሙያ ምዝገባና ፈቃድ ጥያቄ ፎርም፤
2. ከተመረቀበት ኮሌጅ ወይም ዩኒቨርሲቲ የተሰጠ የተማረውን የትምህርት ዓይነትና ትምህርቱን ስለማጠናቀቁ የሚገልፅ ማስረጃ (ሰረተፊኬት፣ ዲፕሎማ፣ ዲግሪ፣ ትራንስክሪፕት)፤
3. የሙያ ብቃት ምዘና ያለፈ መሆኑን የሚያረጋግጥ ሰርተፍኬት (የሙያ ብቃት ምዘና እንዲወስዱ ለተመረጡ የሙያ ዘርፎች)፤
4. ወቅታዊ የሆነ በሙያቸው መመዝገባቸውን የሚያረጋግጥ የሙያ ስራ ፈቃድ (ከዚህ በፊት በሌላ ሀገር እንደ ጤና ባለሙያ ሲሰሩ ለቆዩ ባለሙያዎች)፤
5. የሙያ ብቃትና ስነ-ምግባር ሁኔታን የሚገልጽ አግባብ ያለው የስራ ልምድ (LETTER OF GOOD STANDING) (ከዚህ በፊት በሌላ ሀገር እንደ ጤና ባለሙያ ሲሰሩ ለቆዩ ባለሙያዎች)፤
6. እንግሊዝኛ ተናጋሪ ካልሆኑና ስርዓተ ትምህርታቸው በእንግሊዝኛ ከማይሰጥባቸው አገሮች ለሚመጡ የውጭ ሀገር ዜጎች የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት፤
7. ሶስት ወር ያላለፈውና ባለሙያው ሙያውን ለማከናወን በሚያስችል የጤና ሁኔታ ላይ እንዳለ የሚያረጋግጥ የህክምና ምስክር ወረቀት፤
8. ስድስት ወር ያላለፈው ሁለት ፓስፖርት መጠን ፎቶግራፍ፤
9. የአገልግሎት ክፍያ የከፈለበት ደረሰኝ፤ እና
10. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (2)፣ (4) እና (5) ስር የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ከውጭ ሀገር ለሚመጡ የጤና ባለሙያዎች የሚያቀርቡት ማስረጃ ስልጣን በተሰጠው አካል ህጋዊነቱ የተረጋገጠና በእንግሊዘኛ ቋንቋ ካልሆነ ህጋዊ በሆነ አካል ወደ እንግሊዝኛ የተተረጎመ መሆን ይኖርበታል፡፡

7. የሙያ ስያሜ ስለመስጠት

1. ለባለሙያ የሚሰጥ የሙያ ስያሜ የባለሙያውን የትምህርት ዝግጅት መሰረት ያደረገ ይሆናል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (1) ስር የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ለባለሙያ በሚሰጠው የሙያ ስያሜ ላይ ከስያሜው በፊትም ሆነ በኋላ የአገልግሎት ጊዜን የሚያሳይ ሌላ ቅጥያ ሊኖረው አይገባም፡፡
3. ለባለሙያ የሚሰጠው የሙያ ስያሜ ለዚህ ተብሎ ባለስልጣኑ በሚያዘጋጀው የጤና ባለሙያዎች ዝርዝር ማኑዋል መሰረት ይሆናል፡፡
4. ባለስልጣኑ ለሙያ ስያሜ አሰጣጥ አስቸጋሪ የሆነ ሙያ ሲያጋጥም ከሙያው ጋር አግባብ ያላቸውን የሙያ ማህበራት ወይም የትምህርት ተቋማትን ወይም ባለሙያ ያማክራል፣ በሚያገኘው ሙያዊ አስተያየት መሰረት ውሳኔ ይሰጣል፡፡

8. ስለ ሙያ ስራ ፈቃድ አሰጣጥ

1. ማንኛውም ሰው ለሙያ ስራ ፈቃድ በባለሥልጣኑ የተቀመጡ መስፈርቶችን ካሟላ የሙያ ስራ ፈቃድ ያገኛል፡፡
2. ማንኛውም ሰው የሚያቀርበው የትምህርት ማስረጃ እውቅና ከሌለው የትምህርት ተቋም ከሆነ ወይም ክሊኒካል ለሆኑ ሙያዎች ትምህርቱን የተማረው በርቀት (Distance or Online Education) ከሆነ ተቀባይነት የለውም፡፡
3. ባለስልጣኑ በጤና ሙያ መስክ ለመሰማራት ጥያቄ የሚያቀርብ የጤና ባለሙያን ማስረጃ በመመርመር የሙያ ስያሜ ይሰጣል፣ ይመዘግባል፣ የሙያ ስራ ፈቃድ ይሰጣል፡፡
4. ማንኛውም የጤና ባለሙያ ከአንድ በላይ በሆኑ የጤና ሙያ መስኮች ለመሰማራት የሙያ ስራ ፈቃድ ለማግኘት ጥያቄ ሲያቀርብ ጥያቄውን መሰረት ያደረገ ሁሉንም ሙያዎች ያካተተ የሙያ ስራ ፈቃድ ማግኘት ይችላል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ሶስት የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የጤና ባለሙያው በእያንዳንዱ ሙያ ለሙያ ምዝገባና ፈቃድ የተቀመጡ መስፈርቶችን ማሟላት ይኖርበታል፡፡
6. ማንኛውም የጤና ባለሙያ ከመጀመሪያ ሙያው በቀጥታ ተዛማጅ የሆነ የሙያ ማሻሻያ ወይም የድህረ ምረቃ ወይም የስፔሻላይዜሽን ስልጠና ከወሰደ መጨረሻ ባገኘው ወይም በፍላጎቱ በመረጠው ሙያ በአንዱ ብቻ ሊመዘገብና የሙያ ስራ ፈቃድ ሊሰጠው ይችላል፡፡
7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሰለጠነበት የሙያ ዘርፍ ከመጀመሪያ ሙያው ጋር በቀጥታ ተዛማጅ ካልሆነ ሁሉንም ሙያዎች ያካተተ የሙያ ስራ ፈቃድ ሊሰጠው ይችላል፡፡
8. ማንኛውም በበቂ መጠን በገበያ ላይ የማይገኝ የጤና ባለሙያ ከአንድ በላይ የሙያ ዘርፍ የሰለጠነ ቢሆንና አንደኛው የሙያ ዘርፍ በባለስልጣኑ ሌላው ደግሞ በክልል

የጤና ተቆጣጣሪ አካል የሚመዘገብና የሙያ ስራ ፈቃድ የሚሰጥ ቢሆን ለሁሉም ሙያዎች የሙያ ስራ ፈቃዱ የሚሰጠው በባለስልጣኑ ይሆናል፡፡

9. ማንኛውም ሰው በቀጥታ የጤና ሙያ ዘርፍ ባልሆኑ የሙያ ዘርፎች ሰልጥኖ ከጤና ጋር ግንኙነት ያለው ስራ ለመስራት የሚያስችለው የሙያ ስራ ፈቃድ ለማውጣት የሚፈልግ ከሆነ ከሚሰራበት ተቋም በተቋሙ ውስጥ በዘርፉ እንደሚሰራ የሚገልጽ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

10. ባለስልጣኑ ባለሙያው ለእያንዳንዱ ሙያ ያቀረባቸውን ማስረጃዎች ህጋዊና ትክክለኛ ካልሆኑ ጥያቄውን ውድቅ በማድረግ ፈቃዱን መከልከል ይኖርበታል፡፡

11. እክል ለገጠመው ባለሙያ እንደ አግባብነቱ ውስን የሙያ ስራ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፡፡

## 9. ከሙያ ስራ ወሰን ውጭ ስለመስራት

1. ማንኛውም የጤና ባለሙያ ከተመዘገበበት የሙያ ስራ ወሰን ውጪ የጤና አገልግሎት መስጠት አይችልም፡፡ ሆኖም በልዩ አስገዳጅ ሁኔታ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሲጠየቅና በባለስልጣኑ ሲፈቀድ ከተመዘገበበት ሙያ ውጪ አገልግሎት መስጠት የሚያስችል ጊዜያዊ የሙያ ስራ ፈቃድ ሊሰጠው ይችላል፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም ማንኛውም የጤና ባለሙያ ከስራ ወሰኑ ውጪ በልዩ አስገዳጅ ሁኔታ ለሚሰጠው ተጨማሪ የጤና አገልግሎት ስልጠና መውሰድ ይኖርበታል፡፡

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም ማንኛውም የጤና ባለሙያ ከስራ ወሰኑ ውጪ በልዩ አስገዳጅ ሁኔታ በባለስልጣኑ የተሰጠውን ተጨማሪ የጤና አገልግሎት ሲያከናውን ለሚፈፅመው ሙያዊ ግድፈት በህጉ መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

4. ከባለስልጣኑ በልዩ አስገዳጅ ሁኔታ በጤና ባለሙያው እንዲከናወኑ የሚሰጡ ተጨማሪ የጤና አገልግሎቶች በፅሁፍ የተደገፉ ሆነው በባለሙያው ቢከናወኑ በህብረተሰቡ ጤና ላይ ጉዳት የማያስከትሉና በባለሙያው በብቃት ይከናወናሉ ተብለው የታመንባቸው ብቻ መሆን አለባቸው፡፡

## 10. ስለ አዳዲስ የሙያ ዘርፎች

ባለስልጣኑ በዝርዝር ከለያቸው ውጪ ለሙያ ስያሜ የሚቀርቡ አዳዲስ የሙያ ዘርፎች ለህብረተሰቡ ከሚያስገኙት አዎንታዊ ፋይዳ ጋር እየተነፃፀረ በዚህ መመሪያ አንቀፅ (7) ንዑስ አንቀፅ (4) መሰረት ይስተናገዳሉ፡፡

11. የሙያ ስራ ፈቃድ ስለማሳደስ

1. ማንኛውም የጤና ባለሙያ የተሰጠውን የሙያ ፈቃድ በየአምስት ዓመቱ ማሳደስ አለበት፡፡
2. ማንኛውም የጤና ባለሙያ የተሰጠውን የሙያ ስራ ፈቃድ የጊዜ ገደብ ከመጠናቀቁ አንድ ወር በፊት የእድሳት ጥያቄ ማቅረብ አለበት፡፡
3. ለሙያ ፈቃድ እድሳት የሚያመለክት ባለሙያ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡-

   ሀ. በትክክል የተሞላ የማመልከቻ ቅጽ፤

   ለ. ከዚህ በፊት የተሰጠ የሙያ ስራ ፈቃድ፤

   ሐ. የሙያ ብቃትና ስነ-ምግባር ሁኔታን የሚገልጽ ከሚሰራበት ተቋም አግባብ ባለው ኃላፊ የተጻፈ የስራ ልምድ፤

   መ. በህጉ ላይ የተቀመጠውን ተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ መውሰዱን የሚያረጋግጥ ማስረጃ፤

   ሠ. ሶስት ወር ያላለፈው ሙያውን ለማከናወን በሚያስችል የጤና ሁኔታ ላይ እንዳለ የሚያረጋግጥ የህክምና ምስክር ወረቀት፤

   ረ. ስድስት ወር ያላለፈው ሁለት ፓስፖርት መጠን ፎቶግራፍ፤ እና

   ሰ. የአገልግሎት ክፍያ የተከፈለበት ደረሰኝ፡፡
4. ከአንድ ሙያ በላይ ለመስራት የሙያ ስራ ፈቃድ ያገኘ ባለሙያ ለእያንዳንዱ ሙያ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተቀመጠውን መስፈርት ማሟላት አለበት፡፡
5. ትምህርቱን በውጭ ሀገር ያጠናቀቀ፤ በባለስልጠኑ የሙያ ስራ ፈቃድ የተሰጠውና በሀገር ውስጥ የሚሰራ በበቂ መጠን በገበያ ላይ የሚገኝ ኢትዮጵያዊ የጤና ባለሙያ የሙያ ስራ ፈቃዱን የሚያሳድሰው በሚሰራበት ክልል በሚገኝ የክልል ጤና ተቆጣጣሪ አካል ይሆናል፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ስር በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ የሙያ ስራ ፈቃዱ ያላሳደሰ ባለሙያ ከአምስተኛው ዓመት መጨረሻ ቀን ቀጥሎ ባለው ቀን ጀምሮ ከእድሳት የአገልግሎት ክፍያው በተጨማሪ በየወሩ ለእድሳት የተቀመጠውን የክፍያ መጠን ቅጣት በመክፈል ለሚቀጥሉት ስድስት ወራት ማሳደስ ይችላል፡፡
7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (1)፣ (2) እና (5)መሠረት ሳያሳድስ የቀረ ባለሙያ ያለ ሙያ ስራ ፈቃድ እንደሰራ ተቆጥሮ ባለስልጣኑ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፡፡

12. የተሰጠ የሙያ ስራ ፈቃድ የማይሰራበት ጊዜ

1. ማንኛውም የጤና ባለሙያ በተሰጠው የሙያ ስራ ፈቃድ ከሁለት ዓመት በላይ በማንኛውም ምክንያት በሙያው ሳይሰራ ከቆየ በሙያው መስራት አይችልም፡፡

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሰረት ለባለስልጣኑ ሳያሳውቅ በሙያው ሲሰራ ቢገኝ ባለሙያው ያለሙያ ስራ ፈቃድ ሲሰራ እንደተገኘ ተቆጥሮ ባለስልጣኑ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፡፡

3. ባለስልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ከሙያው ተለይቶ ለቆየ ባለሙያ እንደ አግባብነቱ ከሚከተሉት አንዱን ወይም ከአንድ በላይ እንዲያሟላ ሊወስን ይችላል፡-

    ሀ. ተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ መውሰዱን የሚያረጋግጥ ማስረጃ እንዲያቀርብ፣

    ለ. ስልጠና እንዲወስድ፤ እና

    ሐ. ባለስልጣኑ በሚመርጠው የጤና ተቋም ልምድ ባለው የጤና ባለሙያ ስር ለተወሰነ ጊዜ በክትትል እንዲሰራ፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) (ሐ) መሰረት የጤና ባለሙያ በበሳል ባለሙያ ክትትል ስር ለተወሰነ ጊዜ እንዲሰራ የሚደረገው፡-

    ሀ. በሰለጠነበት የሙያ ዘርፍ ከ ሁለት ዓመት በላይ ሳይሰራ ከቆየ፡

    ለ. በሰለጠነበት የሙያ ዘርፍ እስከ አምስት ዓመት ሰርቶ ከሶስት ዓመት በላይ ሳይሰራ ከቆየ፤

    ሐ. በሰለጠነበት የሙያ ዘርፍ ከአምስት ዓመት እስከ አስር ዓመት ሰርቶ ከአራት አመት በላይ ሳይሰራ ከቆየ፤

    መ. በሰለጠነበት የሙያ ዘርፍ ከአስር ዓመት እስከ ሀያ ዓመት ሰርቶ ከአምስት አመት በላይ ሳይሰራ ከቆየ፤ እና

    ሠ. በሰለጠነበት የሙያ ዘርፍ ከሀያ ዓመት በላይ ሰርቶ ቢያንስ ከስድስት አመታት በላይ ሳይሰራ ከቆየ ብቻ ይሆናል፡፡

5. አንድ የጤና ባለሙያ ልምድ ባለው የጤና ባለሙያ ስር በክትትል የሚቆይበት ጊዜ በሰንጠረዥ1 በተመለከተው መሰረት ይሆናል፡፡

ሰንጠረዥ1. አንድ ባለሙያ በልምድ ባለው የጤና ባለሙያ ስር በክትትል የሚቆይበትን ጊዜ የሚያሳይ ሰንጠረዥ፡፡

| ተ.ቁ | ባለሙያው ከሙያው ተለይቶ የቆየበት ጊዜ | በበሳል ባለሙያ ስር በክትትል የሚቆይበት ጊዜ |
|---|---|---|
| 1. | ከሁለት ዓመት በላይ እስከ አራት ዓመት | ለሶስት ወር |
| 2. | ከአራት ዓመት በላይ እስከ ስድስት ዓመት | ለስድስት ወር |
| 3. | ከስድስት ዓመት በላይ እስከ አስር ዓመት | ለዘጠኝ ወር |
| 4. | ከአስር ዓመት በላይ እስከ አስራ አምስት ዓመት | ለአንድ ዓመት |
| 5. | ከአስራ አምስት አመት በላይ | በጤና ባለሙያነቱ መስራት የለበትም |

6. በዚህ አንቀጽ የተጠቀሱትን አሟልቶ የተገኘ ባለሙያ የሙያ ስራ ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡

13. በውጭ ሀገር የሰለጠኑ የጤና ባለሙያዎችን በኢንተርንሽፕ ስለመመደብ

1. ከመሰረታዊ የጤና ሙያ ስልጠናው ጀምሮ በውጪ ሀገር ስልጠና ወስዶ ለሙያ ምዝገባና ፈቃድ ጥያቄ የሚያቀርብ ማንኛውም ሰው በሰለጠነበት ሀገር ኢንተርንሽፕ ሳይሰራ ወይም በሙያው ከሁለት ዓመት በላይ አገልግሎት ሳይሰጥ የመጣ ባለሙያ ከስድስት ወር እስከ አንድ ዓመት የሚቆይ ኢንተርንሺፕ እንዲሰራ ይደረጋል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው የኢንተርንሺፕ ቆይታ ጊዜው በሰንጠረዥ 2 በተመለከተው መሰረት ይሆናል፡-

ሰንጠረዥ2. በውጪ አገር ሰልጥነው ለሙያ ምዝገባ የሚቀርቡ ባለሙያዎች በኢንተርንሺፕ የሚቆዩበትን ጊዜ የሚያሳይ ሰንጠረዥ፡፡

| ተ.ቁ | የሙያ ዓይነት | የኢንተርንሺፕ የቆይታ ጊዜ |
|---|---|---|
| 1. | ጠቅላላ ሀኪም | አንድ ዓመት |
| 2. | ስፔሻሊስት ሀኪም | ስድስት ወር |
| 3. | ከሀኪም ውጭ የሆኑ ሌሎች ክሊኒካል የሙያ ዘርፎች | ስድስት ወር |

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሰረት ባለሙያው ኢንተርንሺፕ የወሰደ ወይም በሙያው ያገለገለ ቢሆንም የተማረበት አገር የበሽታ ሥርጭት ከኢትዮጵያ የበሽታ ሥርጭት ጋር የማይጣጣም ከሆነ በሰንጠረዥ 3 መሰረት የኢንተርንሺፕ ፕሮግራም ማጠናቀቅ ይኖርበታል፡፡

ሰንጠረዥ3. የተማሩበት አገር ከኢትዮጵያ የበሽታ ስርጭት ጋር ላልተጣጣመ ባለሙያዎች በኢንተርንሺፕ የሚቀዩበትን ጊዜ የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| ተ.ቁ | የሙያ ዓይነት | የኢንተርንሽፕ የቆይታ ጊዜ |
|---|---|---|
| 1. | በተማረበት ሀገር ኢንተርንሺፕ የሰራ ጠቅላላ ሀኪም | ስድስት ወር |
| 2. | ስፔሻሊስት ሀኪም | ሶስት ወር |
| 3. | ከሀኪም ውጭ የሆኑ ሌሎች ክሊኒካል የሙያ ዘርፎች | ሶስት ወር |

4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)፣ (2) እና (3) ድንጋጌዎች ቢኖሩም ባለሥልጣኑ ከውጪ ሀገር ለአጭር ጊዜ በሚቆይ የእርዳታ ስራ፣ ለአደጋ ጊዜ የሰብአዊ እርዳታ ወይም በባለሥልጣኑ በሚወሰኑ ለሌሎች ጤና አገልግሎቶች ለሚመጡ ባለሙያዎች ከሁለት ዓመት በላይ አግባብ ያለው የስራ ልምድ እስካቀረቡ ድረስ ኢንተርንሺፕ ሳያስፈልግ ጊዜያዊ የሙያ ስራ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፡፡

5. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 4 እንደተጠበቀ ሆኖ የጤና ባለሙያውን በጊዚያዊነት ያስመጣው ተቋም

   ሀ) ባለሙያው ተልዕኮውን ሲያጠናቅቅ ወዲያወኑ ለባለሥልጣኑ የማሳወቅና ፈቃዱ እንዲመልስ የማድረግ ሃላፊነት አለበት፡፡

   ለ) ባለሙያው በሚሰጠው የጤና አገልግሎት ለሚያደርሰው የሙያ ስሕተትና ጉዳት አግባብ ባላቸው ሕጎች ተጠያቂ ይሆናል፡፡

14. ምትክ የሙያ ስራ ፈቃድ ስለመስጠት

1. ማንኛውም የሙያ ስራ ፈቃዱ የተበላሸበት ወይም የጠፋበት ወይም የተቃጠለበት ሰው ምትክ የሙያ ስራ ፈቃድ እንዲሰጠው መጠየቅ ይችላል፡፡
2. ማንኛውም ሰው ምትክ የሙያ ስራ ፈቃድ ለማግኘት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች ማሟላት አለበት፡፡

   ሀ) የሙያ ስራ ፈቃዱ የተበላሸ ከሆነ የተበላሸውን የመመለስ፤

   ለ) የሙያ ስራ ፈቃዱ የጠፋ ወይም የተቃጠለ ከሆነ የጠፋ ወይም የተቃጠለ መሆኑን ከፍትህ አካል ማረጋገጫ ማምጣት፤

ሐ) ስድስት ወር ያላለፈው ሁለት የፓስፖርት መጠን ፎቶግራፍ፤ እና

መ) የአገልግሎት ክፍያ የተከፈለበት ደረሰኝ፡፡

3. ባለስልጣኑ የሙያ ፈቃድ ስለመጥፋቱ እና አስፈላጊው ጥንቃቄ እንዲደረግ ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በሰርኩላር ደብዳቤ የማሳወቅና የማሳሰብ እንዲሁም. ለባለሙያው ምትክ የሙያ ስራ ፈቃድ የመስጠት ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

## ክፍል ሶስት
## ስለ አስተዳደራዊ እርምጃዎች

### 15. አስተዳደራዊ እርምጃ ስለመውሰድ

ማንኛውም የጤና ባለሙያ የሙያ ስራ ፈቃድ የሚያሳግድ ወይም የሚያሰርዝ ወይም በወንጀል የሚያስጠይቅ ጥፋት ፈፅሞ ቢገኝ ባለስልጣኑ እንደ አግባብነቱ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል ወይም የወንጀል ክስ እንዲመሰረት ሊያደርግ ይችላል::

### 16. የሙያ ስራ ፈቃድ የሚሳያግዱ ጥፋቶች

ማንኛውም የጤና ባለሙያ ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ ባለስልጣኑ የሙያ ስራ ፈቃዱን ሊያግድ ይችላል፡፡

1. የዚህ መመሪያ አንቀጽ (11) ንዑስ አንቀጽ (6) እንደተጠበቀ ሆኖ በሰለጠነበት የጤና ሙያ ሳይመዘገብ ወይም የሙያ ስራ ፈቃድ ሳይኖረው ወይም ሳያሳድስ የጤና ባለሙያነት ስራ ሲሰራ ቢገኝ እንደ አግባቡ ከስድስት ወር ላልበለጠ ጊዜ፤
2. ከሁለት ጊዜ በላይ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ተገቢውን ማስተካከያ ሳያደርግ ሲቀር እንደ አግባቡ ከሶስት ወር ላልበለጠ ጊዜ፤
3. ባለሙያው በሙያው ለማገልገል ብቃት የጎደለው መሆኑ አግባብ ባለው አካል ሲረጋገጥና ሲወሰን፤
4. ባለሙያው በከባድ የአዕምሮ ህመም ምክንያት ሙያውን በሚገባ መወጣት ካልቻለ የጤና ሁኔታው እስከሚሻሻልና በሀኪም እስኪረጋገጥ፤
5. ሆን ብሎ የሙያውን ስነ-ምግባር በሚቃረን ሁኔታ ከተሰጠው የሙያ ስራ ወሰን ወይም የጤና ተቋም ደረጃ በላይ ሲሰራ የተገኘ እንደሆነ እንደ አግባቡ ከአንድ ዓመት ላላነሰ ከሁለት ዓመት ላልበለጠ ጊዜ፤

6. በተሰጠው የሙያ ስራ ፈቃድ መነሻ በኃላፊነቱ በከፈተው የጤና ተቋም ውስጥ ያልተመዘገበ ወይም የሙያ ስራ ፈቃዱ የታገደበትን ወይም የተሰረዘበትን ወይም የሙያ ስራ ፈቃድ ጨርሶ የሌለውን የጤና ባለሙያ ሲያሰራ የተገኘ እንደሆነ እንደ አግባቡ ከሶስት ወር ላላነሰ ከስድስት ወር ላልበለጠ ጊዜ፤

7. ለህብረተሰብ ጤና በሚያሰጋ ሁኔታ የሙያ ብቃት ችግር ወይም የሙያ ስነ ምግባር ግድፈት ምክንያት ክስ በሚቀርብበት ጊዜ ለባለስልጣኑ ቀርቦ ውሳኔ እስከሚያገኝ፤

8. ባለሙያው በሙያ ስነ-ምግባር ግድፈት ምክንያት አግባብ ባለው አካል እንዲታገድ ሲወሰን፤

9. ለስረዛ የሚያበቁ ግድፈቶች ሲፈጠሩ ጉዳዩ ለፍርድ ቤት ወይም ለባለስልጣኑ ቀርቦ ውሳኔ እስከሚያገኝ፤

10. ከጤና ባለሙያነቱ በታገደበት ወቅት ህገ-ወጥ ጥቅም ለማገኘት ሲል የእገዳ ውሳኔውን ጥሶ የጤና ባለሙያነት አገልግሎት ሲሰጥ የተገኘ እንደሆነ ለተጨማሪ አንድ ዓመት፤

ሊታገድ ይችላል፡፡

17. **የሙያ ስራ ፈቃድን ለመሰረዝ የሚያበቁ ጥፋቶች**

ማንኛውም የጤና ባለሙያ ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ ባለስልጣኑ የሙያ ስራ ፈቃዱን ሊሰርዝ ይችላል፡-

1. የሙያ ስራ ፈቃዱ የተገኘው ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ በማቅረብ መሆኑ በማስረጃ ሲረጋገጥ፤

2. የጤና ሙያ እውቀቱንና ክህሎቱን ተጠቅሞ ከባድ የወንጀል ድርጊት በመፈጸሙ ተከሶ ጥፋተኛነቱ የተረጋገጠ እንደሆነ፤

3. በአንቀጽ (16) ንዑስ አንቀጽ (10) የተጠቀሰውን የእገዳ ቅጣት ተላልፎ የጤና አገልግሎት ሲሰጥ የተገኘ እንደሆነ፤

4. ባለሙያው በሙያ ስነ-ምግባር ግድፈት ምክንያት አግባብ ባለው አካል የሙያ ስራ ፈቃዱ እንዲሰረዝ ሲወሰን፡፡

18. **የሙያ ሥራ ፈቃድ ስለመመለስ**

የሙያ ስራ ፈቃዱ የታገደበት ወይም የተሰረዘበት ወይም በራሱ ፈቃድ ሙያውን የተወ ወይም የመጣበትን ተልእኮ ያጠናቀቀ ማንኛውም ባለሙያ በአስር የስራ ቀናት ውስጥ ፈቃዱን የመመለስ ግዴታ አለበት፡፡

19. **የመተባበር ግዴታ**

ባለስልጣኑ ይህን መመሪያ ለማስፈፀም እንዲችል ጉዳዩ የሚመለከታቸው ማንኛውም የፌደራል እና የክልል መንግስት አካላት የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

## 20. ተፈፃሚነት የማይኖራቸው መመሪያዎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ፣ ሰርኩላር ደብዳቤ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## 21. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ሰኔ 1/2006ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

የሁሉ ደነቀው

ዋና ዳይሬክተር
የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ
አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን

Fill the application form in Amharic only or both in Amharic and English.

